# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በቴክኖሎጂ የሚታገዘው የጊቤ-III ኦፕሬሽን ክፍል

ከዘመኑ ጋር እየዘመነ በሚሄደው ዓለም የሰው ልጆችን አሠራርና አኗኗር የሚያቀሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እየተዋወቅን የመምጣታችን ጉዳይ የተለመደ ነው። የሰው ልጅ እንጨትን አፋትጎ፤ ድንጋይን አፋጭቶ እሳትን በማዋለድ ለምግብ ማብሰያነት እና ለብርሃን ምንጭነት ሲጠቀምበት ከኖረ በኋላ የእሳትን ሚና በኤሌክትሪክ መተካት የሚያስችል ጥበብ ተጎናጽፏል። ዛሬ ኤሌክትሪክ የእሳት እና የብርሃንን ሚና ከመተካት አልፎ ዓለማችንን በሁሉም ዘርፍ የሚያንቀሳቅሳት ሞተር እስከመሆን ደርሷል።

ውድ የአምዳችን አንባቢዎች፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን! ባለፈው ሳምንት ጽፀፋችን በአሠራር ጥበቡ፣ በኃይል ማመንጨት አቅሙ፣ በአገራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው፣ በማህበራዊና አካባቢያዊ አስተዋጽኦው፣ በጥናትና ምርምር ሥራዎቹ፣ በራሱ የሰው ኃይል የጥገና ሥራዎችን በማከናወኑ ወዘተ ተምሳሌትና ተጠቃሽ ስለሆነው የጊቤ-III የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ፤ ሥራ አስኪያጁ ኢንጂነር ሀብታሙ ሰሙ የሰጡንን መረጃ መሠረት አድርገን ያዘጋጀነውን ጽፀፍ ማስነበባችን ይታወሳል።

በዛሬው ዝግጅታችንም የጣቢያው የኦፕሬሽን ክፍል አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል የምናስቃኛችሁ ይሆናል። መረጃውን የሰጡን ኢንጂነር ቢኒያም መብራት የጊቤ-III የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የኦፕሬሽን ክፍል ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እንደኢንጂነሩ ገለጻ ጣቢያው ለአገሪቱ የኃይል አቅርቦት ጉልህ ድርሻ እያበረከተ የሚገኝ፣ ረቂቅ የቴክኖሎጂ ዐሻራ ያረፈበት እና አስር ኃይል የሚያመነጩ ዩኒቶች ያሉት ግዙፍ ጣቢያ ነው።

ኃይል ማመንጫው የጥገና እና የኦፕሬሽን ክፍል የሚባሉ ሁለት አደረጃጀቶች አሉት። የኦፕሬሽን ክፍሉ ኤሌክትሪክ ከማመንጨት እስከ ማሰራጨት ድረስ ያለውን ሂደት 24 ሰዓት ያለማቋረጥ ይቆጣጠራል። ይህም በ3 ፈረቃዎች በተመደቡ ሙያተኞች ይመራል። የኦፕሬሽን ሙያተኞቹ በየሽፍቱ ሁለት ቦታ ላይ ማለትም በኃይል ማመንጫ እና በማከፋፈያ ጣቢያ (Switchyard) ላይ ተመድበው ዩኒቶቹ በአግባቡ ኤሌክትሪክ የማመንጨት ሥራቸውን እንዲከናውኑ እና የተመረተው ኃይል ወደሚፈለገው ቦታ በአግባቡ እንዲደርስ ያደርጋሉ።

አዲስ አበባ ከሚገኘው ብሔራዊ የኃይል መቆጣጠሪያ ማዕከል በሚሰጥ ትዕዛዝ አማካኝነት ጣቢያው ኃይል እንዲጨን በማድረግ ጭነቱን ላሉት ዩኒቶች በማከፋፈል ሲስተሙን ይቆጣጠራሉ። የእያንዳንዱን ዩኒት አጠቃላይ መረጃ በየ2 ሰዓት ልዩነት እየተከታተሉ ምን ዓይነት ለውጥ እንዳለው ያሳውቃሉ።

በዶክመንት ከሚመዘገበው መረጃ በተለየ መልኩ እያንዳንዱ ማሽን ላይ በየቀኑ ፍተሻ እና ቁጥጥር በማድረግ የዩኒቶቹን ጤናማነት ከሙቀት፣ ከዘይት ግፊት፣ ከኮሙዩኒኬሽን እና ሌሎች ቴክኒካል መመዘኛዎች አንጻር ተጽዕኖዎችን ለይተው ማስተካከያ እንዲወሰድበት ያደርጋሉ።

በቁጥጥር ሥራው ብልሽት አለባቸው የተባሉ መሣሪያዎችም ወደ ጥገና ክፍል እንዲላኩ የሚደረግ ሲሆን የጥገና ክፍሉም ተገቢውን ጥገና በማድረግ እና በመፈተሽ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል።

የጊቤ-III የውሃ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የአገሪቱ ኃይል የሚመረትበት ሲሆን የሚፈለግበትን ኃይል ማመንጨት እንዲችል ማድረግ የሁልጊዜ ተግባር ነው።

ጣቢያው ከአቅሙ በላይ የሆኑ ችግሮች ሲገጥሙት ለምሳሌ እየሠራ ያለ ዩኒትን ማቆም ቢያስፈልግ፣ የአገሪቱን የኃይል ኔትወርክ እንዳይረበሽ አስቀድሞ ለሚመለከታቸው



ኢንጂነር ቢኒያም መብራት

ኃላፊዎች ያሳውቃል።

እንደኢንጂነር ቢኒያም ገለጻ የጣቢያው ኃይል የማመንጨት አቅም ግድቡ በሚይዘው የውሃ መጠን ይወሰናል። የግድቡ ውሃ መጠን ሲጨምር የማመንጨት አቅሙም ይጨምራል፤ በዚያው ልክ የግድቡ ውሃ መጠን ሲቀንስ የማመንጨት አቅሙም ይቀንሳል። በበጋ ወቅት ግድቡ የሚይዘው የውሃ መጠን ስለሚቀንስ ኃይል የማመንጨት አቅሙም እየቀነሰ ይመጣል። የሚመነጨው ኃይል ከውሃው መጠን ጋር እየተናበበ በመሆኑ የግድቡ የውሃው መጠን በየዕለቱ ይለካል፤ ይነበባል። በዚህም ከውሃው መጠን ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል እንዲመነጭ ይደረጋል ማለት ነው።

ጊቤ-III 1ሺህ 870 ሜጋ ዋት ኃይል የማመንጨት አቅም ያለው ቢሆንም ዩኒቶቹ ላይ ጫና ላለመፍጠር እና ውሃውን ቆጥቦ ለመጠቀም ሲባል በዚህ ልክ እንዲያመነጭ አይደረግም፤ ወደ ተርባይኖቹ የሚገባው ውሃ መጠኑ በበዛ ጊዜ ጫና ይፈጥራል፤ መጠኑ ባነሰ ጊዜም አየር ስለሚገባ ተርባይኑን ሊጎዳው ይችላል። ስለዚህ የሚጠቀመው ውሃ የተመጠነ ሊሆን ግድ ይላል።

ኃይል ማመንጫው አዲስ እንደመሆኑ አሁን ላይ ዓለም በዘርፉ የደረሰባቸውን ቴክኖሎጂዎች አሟልቶ እየተጠቀመ ይገኛል። ጣቢያው አዲስ አበባ ከሚገኘው ብሔራዊ የኃይል መቆጣጠሪያ ማዕከል ጋር እየተናበበ ይሠራል። ማዕከሉ በጣቢያው የሚገኙ ሁሉንም ሲስተሞች መመልከትና መቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ስላለው በቅርበት ካሉ ሙያተኞች ጋር ስለ እያንዳንዱ ጉዳይ መነጋገር ያስችለዋል።

እንደኢንጂነር ቢኒያም ገለጻ በማሽኖች መገኛ ቦታ ያለውን ከፍተኛ ሙቀት በመቆጣጠር ዕድሜያቸውን ለማርዘም የሚያስችሉ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው። ለዚህም ትልልቅ የሙቀት ማቀዝቀዣዎችን (ቬንትሌተሮችን) በመጠቀም ችግሩን ለመቅረፍ መታሰቡን ተናግረዋል።

ከቴክኖሎጂ ሽግግር አንጻር አዳዲስ ሠራተኞች ወደ ተቋሙ ሲመጡ ወይም ነባር ሠራተኞች ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ በየጊዜው በማሽኖች አጠቃቀምና አያያዝ ዙሪያ ስልጠናዎች ይሰጣቸዋል። በጣቢያው የጥናትና ምርምር ማዕከል እንዲከፈት ያስገደደው አንዱ ምክንያት ይህ ነው።

ጣቢያው የዕውቀት ክፍተትን መሙላት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ የዘወትር ተግባሩ ነው። አንድ ሰው ለመኖር ወይም ለማደግ ዕለት ተዕለት ምግብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የኤሌክትሪክ ኃይልም ለአንድ አገር ዕድገትና ህልውና ወሳኝ ጉዳይ እንደሆነ የተናገሩት ኢንጂነር ቢኒያም ጣቢያው የተጣለበትን አገራዊ ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ በኦፕሬሽን ዘርፍ ያሉ ሙያተኞች ይህን ታሳቢ በማድረግ ሥራቸውን በትጋት ይሠራሉ ብለዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል